የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY
☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:- [illegible]@ethionet.et

ቁጥር Ref. No መሕ/3/90/2003
ቀን Date 08/04/2003

# በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)
# 5ኛ የዓለም አቀፍ ፌዴራሊዝምን አስመልክቶ
# የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

## መግቢያ

የፌዴራሊዝም ዋነኛው እሴት ብዙ ብሔረሰቦች ባሉበት ሀገር ልዩነቶችን በማቻቻል፣ እኩልነትን፣ ነፃነትን እና አንድነትን በማስፈን ልማትን ማፋጠን እና በሕዝብ ሕይወት ውስጥ የተሻለ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ፌዴራሊዝም ሰባት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

1. **አንድነትን ማጠናከር፡-** ኢትዮጵያ ለብዙ ሺህ ዘመናት በመንግሥታዊ ሥርዓት፣ በጋብቻ፣ በባሕል፣ በንግድ፣ በኤኮኖሚ፣ እና በሥነ-ምድር ተሳስራ በነጻነት የቆየችና በሕዝቧ ደምና አጥንት የተገነባች አንድት ሀገር በመሆኗ ኢህአዴግ አንዱን ብሔረሰብ በሌላው ላይ ለማነሳሳት ቢሞክርም አንድነታችንን ሊያናጋ አልተቻለውም፡፡

የእኛ በብሔረሰቦች ላይ የተመሠረተ ፌዴራሊዝም ለአፍሪካም ሆነ ለሌሎች ሀገሮች ጥሩ አርአያ መሆን አይችልም፡፡ እስካሁን አንድነታችን መናጋት ያልቻለው ለብዙ ሺህ ዘመናት በፈጠርነው ውህደት ምክንያት ተፈቃቅረንና ተቻችለን በመግባባት ለመኖር በመቻላችን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በሌላው አፍሪካ ሀገሮች የለም፡፡ በጥሩ ምሳሌነት ሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ናይጀሪያ፣ ወዘተ… የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

2. **እኩልነትን ማስፈን፡-** የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ቀድሞ ከነበረው የተሻለ እኩልነት በኢትዮጵያ አስገኝቷል ለማለት የሚያስችል አስተማማኝ ተግባር አልታየም፣ የለምም፡፡ ለምሳሌ፤ በየትኛውም የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማሕበራዊ መስክ አንድ ብሔረሰብ በሌሎች ሁሉ ላይ የበላይነት እንዲኖረው ጥረት እየተደረገ ያለበት ሀገር ሆነናል፤ ምንም እንኳ ለጥቂት ግለሰቦች ካልሆነ በስተቀር ለብሔረሰቡ የተረፈው አመርቂ እሴት ባይኖርም!

3. **ግጭትን ማስወገድ፡-** የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ግጭትንም አላስወገደም፤ እንዲያውም አባባሰው እንጂ፡፡ ከ20 ዓመታት በፊት ባብዛኛው ሰሜን የሀገራችን ክፍል ላይ ተወስኖ የነበረው የመገንጠል እንቅስቃሴ ዛሬ በአዲስ አበባ እና በሀደሬ መስተዳደሮች በስተቀር ግጭት የሌለበት የሀገራችን ክፍል የለም፡፡ በአራቱም ማዕዘናት የመገንጠል እንቅስቃሴ ጨምሮአል፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ" ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

4. <u>ዴሞክራሲን ማጎልበት</u>፡- የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ሕዝባችንን በምርጫ ከዳር እስከ ዳር በነፃነት ማሳተፍ አልቻለም፡፡ ሕዝባችን ነፃ እና ፍትሐዊ ምርጫ እንዲያደርግ አልተፈቀደለትም፡፡ ማስፈራቱ፣ ድብደባው፣ እስራቱ እና አልፎ አልፎም ግድያው ቀጥሏል፡፡ ከኢህአዴግ ውጭ ተፎካካሪዎችን የደገፈ እና አባል የሆነ ከግብርና ቦታው እና ከመንግሥታዊ ሥራ መፈናቀሉ ዛሬ ከምን ጊዜውም በላይ እንደ ሕግ/ደንብ የተወሰደበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ ይህ የዴሞክራሲ መጎልበትን ሳይሆን ወደ ኃላ መመለስን ነው የሚያሳያው፡፡

5. <u>ሰብዓዊ-መብት ማስፈን</u>፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰዎች በመሆናችን ብቻ መንግሥት ሊሰጠን እና ሊነሳን የማይችል የተፈጥሮ መብቶች አሉን፡፡ እነዚህም በነፃነት የማሰብ፣ በነፃነት የመናገር፣ በነፃነት የመጻፍ፣ በነፃነት የመሰብሰብ እና በነፃነት የመደራጀት ናቸው፡፡ እነዚህን መብቶች የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት የሚፈቅድ ቢሆንም በተግባር ግን ሊተገበሩ አልቻሉም፡፡

6. <u>የሕግ-የበላይነት ማረጋገጥ</u>፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት ከሕግ በላይ ሆነዋል፡፡ የፍትሕ አካላት ማለትም ዳኞች፣ አቃቤያን እና ፖሊሶች፣ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ፣ የመከላከያ ኃይላችን እና የሕዝብ መገናኛዎቻችን በኢህአዴግ ቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ፍትሕ በሁሉም ደረጃ እና የሕብረተሰብ ክፍሎች እንዳይኖር አድርገውታል፡፡ በማናቸውም ደረጃ የኢህአዴግን ሥልጣን የሚፈታተን ከሆነ ማንኛውም ዳኝነት ፍትሐዊ መሆን አልቻለም፡፡ የ1997 እና የ 2002 ዓ.ም ሀገር አቀፍ ምርጫዎች ዋና ምስክሮች ከመሆናቸውም በላይ በእያካባቢው ፍትሀዊ ዳኝነት አለመኖር ይኸንኑ የሚያመለክት ነው፡፡

7. <u>ልማትን ማፋጠን</u>፡- ከሁሉ በላይ የሕዝብን የኑሮ ደረጃ በማሻሻል እና የሕዝብን ሕይወት በመለወጥ የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ያመጣው የተሻለ ሁኔታ የለም፡፡ በተቃራኒው ከ 2-4 ሚሊዮን ረሀብተኛ የነበረው ባለፉት 20 ዓመታት ወደ 7-14 ሚሊዩን ረሀብተኛ ሕዝብ ከፍ ብሏል፡፡ በተጨማሪም በሕዝባችን መካከል ያለው የገቢ ልዩነት ከምን ጊዜውም በላይ ሰፍቶአል፡፡

ስለዚህ በሰባቱም ዋና መለኪያዎች የኢትዮጵያ የብሔረሰቦች ፌዴራሊዝም አርአያነት የለውም፡፡ በተቃራኒው ብሔራዊ ፌደራሊዝም ጊዜው ያለፈበት እና ሁሉም የዓለም ህብረተሰቦች ከሲዊዘርላንድ በኂላ ያለተቀበሉት ሥርዓት ሲሆን የመድበለ ፓርቲ ፌዴራሊዝም ግን ከዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ጀምሮ በዓለም ዙሪያ በሁሉም ሀገሮች የሰራ ፍቱን ሥርዓት በመሆኑ በእኛም ሀገር አስተማማኝ የመድበለ ፓርቲ ፌደራሊዝም ሥርዓት ብቻ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በትግላችን ለዘላዓለም ትኖራለች!

